# ኢሳት ይስማ! ግንቦት 7'ም ልብ ብሎ ያድምጥ!

የጽሑፉ ይዘትና ዓላማ:

ጽሑፉ ሁለት ዓይነት መልዕክቶች አጣምሮ የያዘ ሲሆን በዋናነት ኢሳትም ሆነ የኢሳት ባለቤት የሆነው ጽንፈኛ የፖለቲካ ድርጅት ግንቦት ሰባት በማወቅም ሆነ ባለ ማወቅ የዘነጉትና ልብ ያላሉት ስለ እኛ አዲሱ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከሰሜን እስከ ደቡብ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ያለን እኩል የሆነ አመለካከትና እምነት እንዲሁም ፍጹም ፍቅር ያውቁ ዘንድ፤ በተጨማሪም በኢሳት ፊት አውራሪነት በአንድ ክልልና ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ እየተዘራ ያለው መረራ ዘርና ከዚህም የተነሳ በምድሪትዋ ላይ እያጠላ ያለው መጨረሻው የማያምር የጥፋት ደመናና የእልቂት ምዕራፍ የማስቆም፣ የመቃወምና በቃ! የማለት ድርሻ ለአንድ ወገን ብቻ የሚተው ዓይነት ነገር ሳይሆን የዜጎች ሁሉ ግዴታ እንደሆነ ለማሳወቅ ተፃፈ።

ሐተታ

አንድ ሰው "ምናዊ ነህ"/ከየት ነህ? ተብሎ አገሩ/ዜግነቱ ሲጠየቅ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ብሎ ሲያበቃ በተመሳሳይ *ስለ ትግራይ ሕዝብም ሆነ ስለ ትግራይ ክልል ግን ኢያገባኝም/ኢይመለከተኝም* በማለት መልስ የሚሰጥ ሰው ይኖር ይሆን? (ስለ አማራ ስለ አሮሞና ሌሎች ክልሎችም እንዲሁ) በእርግጥ ከዚህ ቀደም የፈለገውን ያህል በሥልጣን ካለው መንግሥት ጋር የከረረ ጸብና የለየለት አለመግባባት ቢኖረንም ወንበሩን የተቆናጠጡት ጥቂት የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ግለሰቦች ናቸውና ትልቁም ትንሹም የትግራይ ደም ያለበት የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ፍጥረት የሆነ ሁሉም ጠላታችን ነው የሚል አቋምና አስተሳሰብ አልነበረንም ምክንያቱም እንዲህ ያለ ምክንያታዊ ያልሆነ አስተሳሰብ በባለ አእምሮ ሰው ዘንድ የጤና አይደለምና።

እንግዲህ ወደድንም ጠላንም ኢትዮጵያን ለማተረማመስና ዜጎችን ለማጨራረስ በቃላት ብዛት ሰሚ ጆሮ በማሰላቸውት ላይ የሚገኘው ግንቦት 7 በመባል የሚታወቀው ጽንፈኛ ኃይል ድምጹን የሚያስተጋባበትና ከበላይ ሆኖም የሚያስተዳድረው/የሚዘውረው ኢሳት የሳይበር ቴሌቪዥንና ሬድዮ ጣቢያ ከላይ ከፍ ስንል የተመለከትነውን አንድ መንግሥታዊ ሥርዓት ከሰፊው ሕዝብ ነጥለህ የማየት "ጨዋ" አስተሳሰብ አብቅቶለት በአንፃሩ ልዩነት ለግልሰቦች የሥልጣን ጥም ማርኪያ ወደሚሆንበት አቅጣጫ ተቀይሶ ሰዎች ከቋንቋ ልዩነትቶቻቸው የተነሳ ወደ አላስፈላጊ ሁከትና ትርምስ ይገቡ ዘንድ ደም ለመቃባት፣ አንዱ በሌላው ወገኑ እንዲነሳና ሆ ብሎም ጦርነት በማወጅ በቁጥር አነስተኛ በሆነ ሕዝብ ላይ በመዝመት የበላይነቱ እንዲያሳይና እርስ በርሱም ተጨራርሶ እንዲተላለቅ ይህ የሳይበር ቴሌቪዥንና ሬድዮ ጣቢያ በአህጽሮተ ቃል ኢሳት በመባል የሚታወቀው ተቋም ታጥቆ ለመነሳቱ ስንቶቻችን ልብ ብለናል?

ኢሳት ምንም እንኳን ሳያፍር *"የኢትዮጵያ ዓይንና ጆሮ ነኝ"* በማለት ከመደስኮር ባይመለስም መሬት ላይ ያለው ሐቅ ግን እንደሚከተለው ይመስላል። ይህ የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባርም ሆነ ባለ እንጀራህን የመጠበቅና የማክበር ኢትዮጵያዊነት ባህል ፈጽሞ ያላለፈበት ኃላፊነት የጎደለው፣ ተጠያቂነት የማይሰማው፣ ተአማኒነት የሌለውና ጫፍ ይዞ ተራ አሉባልታ በመዝራት ዝናን እያተረፈ የሚገኘው የፕሮፖጋንዳ ማዕከል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ለማውደም እንዲሁም ለማተረማመስ ግንባር ፈጥሮ ያልተሰለፈበት ፀረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውን ኃይሎች የለም። በኃይማኖት ረገድ አንስተን የተመለከትን እንደሆነ ወቅት እየጠበቁ ጎተራቸውን የሚሞሉ፣ አጽራረ ጽድቅና ቅድስና ሆነው ሳሉ መንፈሳዊ ጭንብል አጥልቀው የሚያሽረግዱ፣ በኃይማኖት ስም ሀገርንና ትውልድን ለማጥፋት ተማማለው የወጡ እንደ'ነ "ማኅበረ ቅዳሳን" ያለ ከመጋረጃ በስተጀርባ ተቀምጠ የሚዘውርዋቸው ለምስክርነት የማይበቁ መካነ ድሮች እንዲህ አሉ እያለ ሆነ ብሎ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች መካከል እሳት ለመለኮስ የሚያደርገው አንዱ የተቋሙ የዘቀጠ ሞያዊ ግጽታው ሲሆን ወደ ፖለቲካ የጥፋት ጥምረቱ ያለፍን እንደሆነም ኢሳት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኢትዮጵያን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት፣ ከሆነለትና ከተሳካለትም ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከካርታ ፍቆ ለማጥፋት የሌሊት እንቅልፍ ያጣ በምሥርቅ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሰላም ማጣት በዋናነት ድፍን አለም ከሚያውቀው ሁከተኛ የኤርትራ መንግሥት የኢሳት ባለቤቶች ያላቸውን ግኙኝነትና አጋርነት በመመልከት ብቻ የኢሳት ጸረ- የትግራይ ሕዝብ አጀንዳው ብቻ ሳይሆን ጸረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለመሆኑ በቀላሉ ማየት ይቻላል።

ኢሳት ይስማ! ግንቦት ሰባትም ልብ ብሎ ያድምጥ! ከማንም አብሩ ከማንንም ተሰለፉ ጥጉ ከእንግዲህ ወዲህ በቀላሉ የሚጠፋ ክልል/ሕዝብ/ጎሳም ሆነ ነገድ ሊኖር እንደማይችል ግን ታውቁ ዘንድ ይፈለጋል። የተሞከረ እንደሆነም ተያይዘን እንተላለቃታለን እንጅ አንዱ ሌላውን አጥፍቶ የበላይነቱን የሚያሳይበትና የሰላም እንቅልፍ የሚተኛበት መንገድ አይኖርም።

አለቆቻችሁ እንደ ጦር ለምትፈሩ ለኢሳት ቅጥረኞ! ወደዳችሁም ጠላችሁም የትግራይ ሕዝብ በራሱ አንደበት *"ከዛሬ ዕለት ጀምሮ እኛ የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆን የትግራይ ክልል ተወላጆች የኢትዮጵያ ሕዝብ ክፍል አይደለንም። ኢትዮጵያ ከምትባል ሀገርም ምንም ዓይነት ዕድል ፈንታ ክፍልም የለንም!"* በማለት ክልሉና የክልሉ ተወላጆች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በማሰማት እስካልተነሱ ድረስ ያለ አንዳች ጭብጥ ከባዶ መሬት እየተነሳችሁ የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት የመግፈፍም ሆነ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ሕዝብ ጋራ ቅራኔ ውስጥ የሚያስገባ ማንኛውም ዓይነት የአመጽ ቃል የመናገር መብት የላችሁም። ከእንግዲህ ወዲህ ይህ ሐቅ ተላልፎ እንደልቡ የሚሆን ግለሰብም ሆነ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የተገኘ እንደሆነ ግን ድርጊቱም ወንጀል ነው የድርጊቱ ወጣኝ፣ ፈጻሚ፣ አስተባባሪና ተባባሪም በእኩል ሚዛን ወንጀለኞች ይሆናሉ። ወንጀለኛ በሕግ ፊት ማቅረብ ደግሞ አሁን ገና በእኛ የምንጀምረው ጉዳይ አይሆንም። እንዲህ ያለ ጸረ ሀገርና ጸረ ሕዝብ የሆነ ማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ ማለትም የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት የሚፈታተን አቋም የሚያራምድና የሚያጸባርቅ ኃይልና እኩይ ድምጽ የሚያስተጋባ መሰሪ የመቃወምና የመቋቋም ድርሻ ደግሞ የግድ የትግራይ ክልል ተወላጅ መሆን አይጠበቅብንም። እንዲህ ያለ ዕዳው በቀላሉ ተከፍሎ የማይዘጋ ሒሳብ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ሸክም እንደሆነ ሁሉ ድርጊቱ የመቃወም ድርሻም የሁላችን ኢትዮጵያዊን ዜጎች ግዴታ ይሆናል።

ኢሳት ይስማ! ግንቦት 7'ም እንደሆነ ልብ ብሎ ያድምጥ! እኛ አዲሱ ትውልድ ኢትዮጵያውያን (በቀዳማዊ ጃንሆይ ያልደነቆረ፣ በወታደራዊ የደርግ መንግሥት በሽታ ያልተለከፈና ደሙ ያልተበከለ ትውልድ) ስለ ሀገራችንና ስለ ሕዝባችን በተለይ በአንዳንድ የሥልጣን ጥም የተጸናወታቸው ነፃ ያልወጡ "ነፃ አውጪዎች" ሰለባ ሆኖ ስለሚገኘው የአጥንታችን ፍላጭ የሥጋችን ቁራጭ ስለሆነው የትግራይ ሕዝብ ያለን እምነትና አቋም ይህ ነው።

- የትግራይ ሕዝብ እንደ ሌላው ኢትዮጵያዊ ሕዝብ እኩል የምንሟገትለትና የምንዋደቅለት ሕዝባችን ነው!
- የትግራይ ሕዝብ ህመም ህመማችን ነው!
- የትግራይ ሕዝብ ሐዘን ሐዘናችን ነው!
- የትግራይ ሕዝብ ደስታ ደስታችን ነው!
- የትግራይ ሕዝብ ውድቀት የኢትዮጵያውያን ሁሉ ውድቀት ነው!
- የትግራይ ሕዝብ መለወጥና ማደግ በኢትዮጵያዊነታች የምንኮራ ዜጎች ሁሉ ዕድገት ነው!
- የትግራይ ሕዝብ ጠላት የእኛ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ጠላት ነው!

- ትግራይን ነጥለህ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውነት የለም!
- የትግራይ ሕዝብ የማያሳትፍ/ያላሳተፈ ማንኛውም ዓይነት ትግል ጸረ ኢትዮጵያዊነት ነው!
- የትግራይ ሕዝብ ከአማራ ሕዝብ፣ የአማራ ሕዝብ ከደቡብ ሕዝብ፣ ጉራጌው ከከምባታ በቋንቋ፣ በነገድና በባህል ልዩ ልዩ ቢሆንም ኢትዮጵያዊነታቸው በገዛ ፈቃዳቸው እስካላነሱና እስካልሰረዙ ድረስ ለእነዚህና ሌሎች ክልሎቻችን እኩል ፍቅርና እኩል ልብ ነው ያለ። በተረፈ ተከባብሮ ተቻችሎና ተፋቅሮ ያለና እየኖረ ያለውን/ባለው ሕዝብ መካከል ላይ ለግል ፖለቲካዊ ጥቅም ሲባል እሳት ለመጨርና እርስ በርስ ለማጨራረስም በማኛውም ዓይነት መንገዶች የሚደረጉ የጥፋት ትንኮሳዎችና አላስፈላጊ ቅስቀሳዎች ውሎ አድሮ ሰፋሪው በሰፈረው መስፈሪያ ሳይሰፈርለት እንዲሁ በዋዛ ፈዛዛ "በምሕረት" የሚታለፍ ነገር አይኖርም።

ኢሳት የናፈቀው ወንድም ወንድሙን፣ ወዳጅ የባለጀራውን አንገት እየቀላ ሲጥል፣ ምድሪቱ ወድማ በአንስትና ምንም የማያውቁ ህፃናት ደም ተጨማልቃ፣ የምድሪቱዋ ዘር የሆነው ተባዕት ዜጋ ሥጋው ለምድር አራዊትና ለሰማይ ሠራዊት ሆኖ ማየት ከሆነ ስህተቱ የጣቢያው ሰራተኞች ብቻ ሳይሆን በዋናነት ይህን ደም የማፋሰስና ሀገር የማፈራረስ ስውር ዓላማ አነግቦ እያሽረገደ መሆኑን እያወቅን ሀብታችንና ገንዘባችን በመስጠት ጉልበት እየሆነው የምንገኝ ዜጎች ጭምር ይሆናል።

እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ ኢሳት ማለት:

- ለልማት ሳይሆን ለጥፋት፣
- ለሰላም ሳይሆን ለሁከትና ለጦርነት፣
- ለዕረፍት ሳይሆን ለዋይታና ለለቅሶ፣
- ለአንድነት ሳይሆን አንድ የነበረውን እንደ ሥጋ ቅርጫት ለማበጣጠስና ለመከፋፈል፣
- ለነጻነት ሳይሆን ለባርነት፣
- ለህይወት ሳይሆን ደም ለማፋሰስና ለሞት፣
- ለዕድገት ሳይሆን ለውድቀት፣ ለድቀትና ለውድመት፣
- ለፍትሕ ሳይሆን ለውርደት፣ ፍርደ ገምድልነትና ለአፈና፣
- ከዚህም አልፎ ዲሞክራሲና እኩልነት ለማንገስ የተቋቋመ የዜና ማሰራጫ ማዕከል ሳይሆን በአንጻሩ በኢትዮጵያ ምድር ከዚህ ቀደም በታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ካለው፣ "ሰው መሆን እንደ ወንጀል ይቆጠር ነበር" ተብሎ ከሚነገርለት አንድ ትውልድ ቀጭቶ ካለፈው እግዚአብሔር የለሹ ወታደራዊ መንግሥት የደርግ ዘመን ይልቅም የባሰ፤ ወንድም በወንድሙ አንገት ላይ ወጥቶ የሚሸልልበት የትርምስ ዘመን ለማንገስ የተሰለፈ የዘንዶ ምላስ ለመሆኑ የሚሰማ ጆሮ ላለው ሀገር ወዳድ ዜጋ ምስክርነቴን ለመስጠት እወዳለሁ። በዋናነት ለማስተላለፍ የተፈለገው መልዕክት: ይህን የመሰለ አልሚ መሳይ አውዳሚ የማስቆም፣ የመቃወምና በቃ! የማለት ድርሻ ለአንድ ወገን ብቻ የሚተው ድርሻ ሳይሆን ምርጫ የሌለው የኢትዮጵያውያን ዜጎች ሁሉ ግዴታ ነው! እየተባለ ነው ያለው።

ኢሳት ይስማ! ግንቦት 7'ም እንደሆነ ልብ ብሎ ያድምጥ! አማራ ከትግራይ፣ ኦሮሞ ከአማራ፣ ጉራጌው ከደቡብ፣ ሐረሩም ከሶማል ... እየከፋፈልክ፣ አንዱን ከአንዱ እያበላለጥክ፣ ወገን ከወገን እየገነጣጠልክና እንደ ሥጋ ቅርጫትም

እየመታተርክ ስታበቃ "ኢትዮጵያዊ" ነኝ ማለት ሲበዛ ቀልድ ነው። ቀልድ አለ ስፍራውና አለ ቦታው የገባ ወይም የተነገረ እንደሆነ ደግሞ ዋጋ እንደሚያከፍል ለባለ አእምሮ ብዙ ማለቱ ጊዜን ከማባከን አልፎ የሚፈይደው ቁምነገር አይኖረውም።

ለዛሬ በማስታወስ ጽሑፌን ልቋጭ። አበው እንቢተኛ/አመጸኛ ሰውን በውስጠ ወይራ ሲገስጹ"*ጅብ የሚያነክሰው እስኪታወቅበት ድረስ ነው"* ይላሉ ጅብ የተባለው ትርጓሜው ለማጥቃት የተንሰፈሰው ኃይል ይሁን የተደገሰለት ሕዝብ ለመሆኑ ጊዜ የሚፈታው ጉዳይ ሲሆን ቁምነገሩ ግን አገር ሰላም ነው ብሎ እንደ አንስት አንበሳ በተጋደመ ግለሰብ/ሕዝብ ላይ ስትዶልትና ስትተናኮል ይህን እያሰብክ ይላሉ *"በአናትህ የማይጠፋ እሳት በሆድ እግርህም የማይተኛ ትል የማኖር ያህል እንደሆነ እያሰብክ ግባበት"* እንዲሉ።

ሳምንት

ኢሳት በትግራይ ሕዝብ የከፈተው ጦርነት/ዘመቻ በአስቸኳይ ያቁም! (ክፍል ሁለት)

"ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ነበረች!"

በድሮ ዘመን (በእስራኤል) በምርኮ የሚገኝ ፈረስ ሳይውል ሳያድር ወድያውኑ ቃንጃውን ይቀረጥ ነበር። ይህ ማለት ዳግም ሁለተኛ አንዳይጋልብና ለጥቅምም እንዳይውል ታስቦ ከቁርጭምጭሚቱ በላይ ጅማቱ ይቆረጣል ማለት ነው። ኢሳት ሀገራችን ኢትዮጵያ ለማፈራረስ በተለይ ወገናችን በሆነው በትግራይ ሕዝብ ላይ የከፈተው ጦርነት/ዘመቻ ያቆም ዘንድ ኢትዮጵያዊነታችን ግድ ብሎ ካያለንበት አቅጣጫ ብሔርን መሰረት ያደረጎ የፕሮፖጋንዳ ዘጋባዎቹ በአስቸኳይ እንዲያቆም ድምጻችን ካላሰማን የዚች ምድር ስም በተጠራ ቁጥር "ኢትዮጵያ የምትባል እንዲህ የመሰለች ሀገር ነበረች እየተባለ በትዝታ የሚታወስበትና የሚወራበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

ዲ/ን ሙሉጌታ ወልደገብርኤል
E-mail - yetdgnayalehe@gmail.com
United States of America
February 02, 2013